በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

Federal Democratic Republic of Ethiopia
CIVIL SERVICE COMMISSION

ቁጥር/Ref.No ፌ/ሲሶ/ኮቢ/541/14

ቀን/ Date 26 መጋቢት 2014

በዝርዝሩ ለተመለከቱት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በሙሉ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>በመንግስት ሠራተኞች የድልድል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 859/2014 ላይ ተጨማሪ ውሳኔዎችን ስለማስተላለፍ</u>

የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤቶች መዋቅራዊ አደረጃጀት ለውጥ መሠረት የመንግስት ሠራተኞች የድልድል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 859/2014 ከኮሚሽናችን ህዳር 22 ቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር ሲሰኮ/ኮቢ/463/14 በተጻፈ ደብዳቤ መተላለፉ ይታወሳል።

በዚህም መሰረት መስሪያ ቤቶች መዋቅራዊ አደረጃጀተቻውን እና የስራ መዘርዝሮችን በማዘጋጀትና በማስመዘን በኮሚሽናችን ፀድቆ ለአብዛኛው መስሪያ ቤቶች ስለተላለፈ ወደ ሰራተኛ ድልድል እየገቡ መሆኑ ይታወቃል።

ስለሆነም በየመስሪያ ቤቱ እየተካሄደ ያለው የሰራተኞች ድልድል ያለበትን ደረጃ ለይቶ ለማወቅ፣ ያገጠሙ ችግሮችን መፍትሄ ለመስጠት እንዲቻል ኮሚሽናችን በ18 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የድልድል ሂደቱን በተመለከተ የድጋፍና ክትትል ስራ አከናውኗል። በክትትልና ድጋፍ ሂደቱም ከተለዩት ጉዳዮች ውስጥ በአፈፃፀም መመሪያው ላይ ወጥ ግንዛቤ ያልተያዘባቸውና ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ድንጋጌዎች እንዳሉ መገንዘብ ተችሏል።

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር



ስልክ /Tel +251115 54 96 66/67
ፋክስ /Fax +251 115 54 97 07
Email:- ethiocsc@gmail.com
Website:- www.csc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa Ethiopia
ማገልገል ክብር ነው! ድህነትን ለማሸነፍ ማገልገል ደግሞ ድርብ ክብር ነው!
Serving to Beat Poverty is Double Honor!

በመሆኑም በመመሪያው ያልተሸፈኑና ግልፅኝነት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲገጥሙ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እየቀረበ ውሳኔ የሚሰጥበት ስለመሆኑ በድልድል መመሪያው የተደነገገ ሲሆን በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት ተጨማሪ ሰርኩላር ማስተላለፍ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል።

በዚህም መሰረት፡-

1. የድልድል አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 859/2014 ላይ ከኮሚሽናችን በቁጥር ሲሰኮ/486/14 ጥር 08 ቀን 2014 ዓ.ም በተላለፈው ሰርኩላር ተራ ቁጥር 1 እና 2 ለተመለከተው ተጨማሪ ዝርዝር አፈፃፀም እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል። በመሆኑም፡-

   ሀ) ለቡድን መሪ እና በላይ ለሆኑ የስራ መደቦች ለትምህርት ዝግጅት የሚሰጥ ነጥብ ለሶስተኛ ዲግሪ 40፣ ለሁለተኛ ዲግሪ 36 እና ለመጀመሪያ ዲግሪ 32 እንዲሁም ለስራ ልምድ አግባብነት አስር አመትና በላይ ላለው 25፣ ሰባት አመትና ከአስር አመት በታች 23፣ አምስት አመትና ከሰባት አመት በታች 22 እና ከአምስት አመት በታች 19 ነጥብ በመስጠት እንዲወዳደሩ፣

   ለ) ለቡድን መሪ በታች ለሆኑ የስራ መደቦች ለትምህርት ዝግጅት የሚሰጥ ነጥብ ለሶስተኛ ዲግሪ 55፣ ለሁለተኛ ዲግሪ 51 እና ለመጀመሪያ ዲግሪ 47 እንዲሁም ለስራ ልምድ አግባብነት አስር አመትና በላይ ላለው 45፣ ሰባት አመትና ከአስር አመት በታች 40፣ አምስት አመትና ከሰባት አመት በታች 35 እና ከአምስት አመት በታች 30 ነጥብ በመስጠት እንዲወዳደሩ፣

2. አንድ ሰራተኛ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገር በመስሪያ ቤቱ በተሰጠው የረጅም ጊዜ የትምህርት ዕድል ሙሉ በሙሉ ከስራው ውጪ ሆነው ስለሚቆዩ በትምህርት ላይ የቆየበት ጊዜ በስራ ልምድነት የማይያዝ መሆኑ ታውቆ በዚሁ መሰረት እንዲፈፀም፣

3. በድልድል አፈፃፀም መመሪያው አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ (12) በተቋሙ ተፈቅዶለት አንድ አመት ወይም ከዚያ በላይ የሚቆዩ ሰራተኞችን በተመለከተ፡-

   ሀ) የትምህርት ጊዜውን ለማጠናቀቅ አንድ አመትና በታች የቀራቸውን ሰራተኞች ቀድሞ በነበሩበት የስራ መደብ ወይም ትይዩ በኮሚቴው እንዲመደቡ፣

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Civil Service Commission

ለ) የትምህርት ጊዜውን ለማጠናቀቅ አንድ አመት እና በላይ የቀራቸውን ሰራተኞች ለትምህርት ከመሄዳቸው በፊት ሲሰሩበት የነበረ የስራ መደብና ደረጃ ለትምህርት ሲሄዱ ከተቋሙ ጋር ከገቡት ውል ጋር ታይየዞ ለኮሚሽናችን በማቅረብ ጊዜያዊ የስራ መደብ እንዲፈቀድ እና በዚሁ ላይ እንዲመደቡ እንዲደረግ፣

4. ጡረታ ለመውጣት ስድስት ወራትና በታች የቀረው ሰራተኛ በድልድሉ ተመዝግቦ የማይወዳደር ሲሆን የሰራተኙው መረጃ ለኮሚሽኑ እየተላከ ጊዜያዊ የስራ መደብ እንዲፈቀድ እና በዚሁ ላይ እንዲመደቡ እንዲደረግ፣
5. በድልድል አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ሰራተኞች በሁለቱም መስሪያ ቤት በድልድሉ ተመዝግበው መወዳደር የሚችሉት ቢበዛ በሁለት የስራ መደቦች ላይ ብቻ መሆኑ ታወቆ በዚሁ መሰረት እንዲፈፀም፣

የተወሰነ መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

ግልባጭ

- ለኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለም/ኮሚሽነር ጽ/ቤቶች
- ለሰው ሀብት ህጎች ጥናትና ኦዲት ዳይሬክተር ጄኔራል
- ለሰው ሀብት ህጎች ጥናትና ስርፀት ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ኦዲት ዳይሬክቶሬት

ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

ለከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር

ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

ለማዕድን ሚኒስቴር

ለባህልና ስፖርት ሚኒስቴር

ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

ለጤና ሚኒስቴር

ለቱሪዝም ሚኒስቴር

ለፍትህ ሚኒስቴር

ለግብርና ሚኒስቴር

ለትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር

ለትምህርት ሚኒስቴር

ለገንዘብ ሚኒስቴር

ለውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር

ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

ለሰላም ሚኒስቴር

ለመስኖና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር

ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር

ለሥራና ክህሎት ሚኒስቴር

ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission